# ፖሊሲ

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

**ተዛማጅ የመረጃ ምንጮች:** ACA, ACF, ACF-RA, COA, COA-RA, COB-RA, COC-RA, COE-RA, COF-RA, COG-RA, ECC-RA, IGN, IGO-RA, JGA-RA, JGA-RB, JGA-RC, JGB-RA, JFA, JFA-RA, JHF, JHF-RA, JNA-RB

**ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት:** Office of the Chief of Teaching, Learning, and Schools; School Support and Improvement

## የባህሪ ጣልቃገብነት፣ደህንነት እና የደህና ቁመና እቅድ

A. **ዓላማ**

1. ለትምህርት ውጤታማነት አስፈላጊ የሆኑትን አወንታዊ፣ መከባበር የሠፈነበት፣ በሥርዓት የታነፀ፣ እና ደህንነታቸው የተጠበቀ የትምህርት አካባቢዎችን ለማበረታታት፤ የተማሪዎችን ተሳትፎ ማሳደግ፤ የተማሪዎችን ስኬት ማበረታታት እና የተማሪ እኩይ ተግባርን በተቻለ መጠን ከመከሰቱ በፊት የሚከላከሉ አወንታዊ የት/ቤት ባህል እና በጎና ገንቢ ሁኔታዎችን ማሳደግ።

2. ሁሉንም ተማሪዎች ውጤታማ የሚያደርጋቸው ትምህርት እንዲማሩ ማድረግ እና ትምህርት የሚከብዳቸው ተማሪዎችን ለመደገፍ በተገቢው መንገድ ጣልቃ መግባት። ትምህርት ቤቶች ለመማር የሚመቹ አስተማማኝ ቦታዎች እንዲሆኑ

3. MCPS የተማሪ የስነምግባር ህግጋት ጋር የማይጣጣም የተማሪ ባህሪን ለመቅረፍ ግልጽ፣ተገቢ እና ዘላቂነት ያለው ከመጥፎ ስነምግባር ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ መዘዞችን ለመከላከልና የሚረዳ የሚያድስ፣ የሚጠግን፣ ትምህርታዊ፣ ፍትሃዊ እና በፍትሃዊነት የሚተገበር የባህሪ ጣልቃገብነት ፍልስፍናን ማስረፅ ፣ትምህርት የሚሰጠው በአካል ወይም ቨርቹወል ቢሆንም

4. ስለሚጠበቁት የተማሪ ባህሪያት እና መጥፎ ባህሪ ስለሚያስከትለው መዘዝ ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች እና ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ቤተሰቦች በግልፅ ማሳወቅ

B. **ጉዳዩ**

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ የተማሪዎችን ትምህርት ማበልፀግ ዋና ተግባሩ እንደሆነ ያምናል፤ ስለዚህም ይህ ፖሊሲ ለትምህርት ውጤታማነት ምቹ የሆነ የትምህርት አካባቢን ማጎልበት ላይ የሚያተኩር ሲሆን ተገቢ ባህሪ የሚቀሰሙት/የሚማሩት መሆኑንም ይገነዘባል።

2. ከተማሪው(ዋ) ቤት በተጨማሪ፣ ት/ቤቶች በጋራ መከባበር እና አርአያነት ያለው አዎንታዊ ባህሪ የሚጠበቅባቸው፣ በጥሩ ስነምግባር የታነጹ ማህበረሰቦች ናቸው። ቦርዱ አወንታዊ፣መከባበር የሠፈነባቸው፣ ስነ ሥርዓት የሚከበርባቸው እና ደህንነታቸው የተጠበቀ የመማሪያ አካባቢዎችን ለመመስረት እና ለመጠበቅ አስፈላጊ አጋሮች መሆናቸውን ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች ያረጋግጣል።

3. ጤነኛ፣ ውጤታማ የሆኑ አዋቂዎች ሆነው እንዲያድጉ፣ ተማሪዎች መከባበር የሰፈነበት የትምህርት ምህዳር ይፈልጋሉ፣ ይሄም ማለት እያንዳንዱ ሰው ዋጋ ያለው የማህበረሰብ አባል የሆነበት እና ይሄን ለመፍጠር እና ለማስቀጠል በጎ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው በማመን ነው። የመማር/ማስተማር ማህበረሰብ ሲረበሽ፣ የትምህርት መሪዎች የመስተጓጎሉን መንስኤዎች መረዳት፣ የችግሩን መንስኤ ማወቅ እና ችግሩን በመፍታት፣ የትምህርት አካባቢው ወደ መደበኛ የሥራ እንቅስቃሴ እንዲመለስ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፣ እና ተማሪዎች

ከስህተታቸው እንዲማሩ፣ በስነምግባር ጉድለት የሚደርስ ማንኛውንም ጉዳትና የተበላሹ ነገሮችን እንዲያርሙ እና ግንኙነታቸውን ወደነበረበት እንዲመለሱ እድል ይሰጣቸዋል።

4. ተማሪዎችን የሚያበረታታና የሚያሳትፍ ለትምህርት ምቹ የሆነ አካባቢ ተማሪዎችን ለኮሌጅ እና ለስራ ዝግጁ እንዲሆኑና በትምህርት ቤት እንዲቆዩ ያደርጋል።

C. **ፍልስፍና**

1. አወንታዊ የት/ቤት ድባብን የሚያበረታቱ ትምህርት ቤቶች ሁሉንም ተማሪዎች በትምህርት ላይ ለማሳተፍ እና ትምህርት የሚከብዳቸው ተጋላጭ ተማሪዎችን ለመደገፍ በተገቢው ሁኔታ ጣልቃ ይገባሉ። ይህ የባህሪ ጣልቃገብነት ፍልስፍና እና የሚጠበቁ የተማሪ ባህሪያት እና የመጥፎ ስነምግባር ውጤቶች ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች እና ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ለቤተሰቦች በሥነ ምግባር ደንቦች እና በአፈጻፀም መመሪያ ደንቦች ላይ የሚጠበቁትን ወጥነት ያለው የተማሪ ሥነ ምግባር እና የተማሪ ባህሪ ከተዛባ - እና ህግን ካላከበሩ፤ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተማሪ ስነምግባር ደንብ መጣስ የሚያስከትለውን መዘዝ በግልጽ ማሳወቅ አለባቸው። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ የስነምግባር ደንብ።

2. ሁሉም ተማሪዎች የሚማሩበት ደህንነቱ የተጠበቀ ሥፍራ የማግኘት መብት አላቸው። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ ወይም በትምህርት ፕሮግራሞቹ እና እንቅስቃሴዎች ላይ የተማሪ ስነምግባር ሌሎችን የሚያስፈራራባቸው ሁኔታዎች ከተፈጠሩ ቦርዱ ጉልበተኝነትን፣ትንኮሳን፣ጾታዊ ትንኮሳን፣ ወይም ማስፈራራትን በፖሊሲ/Policy JHF መሠረት ጉልበተኝነት ወይም የወከባ ድርጊቶችን አይታገስም። እንዲሁም የቦርድ ፖሊሲ/Policy ACF ላይ በተደነገገው መሠረት የተማሪዎች የፆታ ብልግና እና ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃትን በትግስት አያሳልፍም።

3. የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy ACA መሠረት አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት፣ እና ባህላዊ ብቃት ጋር በማጣጣም MCPS ትምህርት ቤቶች እና የስራ ቦታዎች ፍትሃዊ፣ደህንነታቸው የተጠበቀ፣የተለያዩ ብዝሃነትን ያካተቱ እና ከአድሎአዊ ጥላቻ፣አመጽ፣እና የንቀት ድርጊቶች የፀዱ ይሆናሉ።

    a) ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን መጠቀም ወይም ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን ማሳየት ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት ወይም የንብረት መውደምን የሚያካትቱ ጉዳዮች ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ የሚያስወስድ ግብረመልስ የመስጠት ደረጃዎችን ከፍ የሚያደርግ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

    b) በዲሲፕሊን ውሳኔዎች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች የተማሪን ዕድሜ፣ የቀድሞ ከባድ የዲሲፕሊን ጥሰቶችን፣ የተማሪን ባህሪ ለመረዳት አውድ ሊሰጡ የሚችሉ የባህል ወይም የቋንቋ ሁኔታዎች፣ ክስተቱን የሚመለከቱ ሁኔታዎች እና ሊደርስ የሚችለውን የከባድ ጉዳት ስጋት ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

4. የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy COA፣ የተማሪ አጠቃላይ ጤና ደስታ እና የትምህርት ቤት ደህንነት፣ እና ፖሊሲ/Policy JPG፣ ጤነኛ ቁመና፣ አካላዊ ጤንነት እና የተመጣጣነ-አመጋገብ እንዲኖር እያንዳንዱ የ MCPS ትምህርት ቤት መጣር አለበት ጥሩ የትምህርት አካባቢን ብቻ ሳይሆን የሚከተሉትን እሳቤዎች ለመተግበር ጭምር የሚያገለግል ልምድና ባህል መፍጠር አስፈላጊ ነው –

    a) በከፍተኛ ተነሳሽነት ቶሎ ምላሽ የሚሰጥ የመልካም ግንኙነት ባህል መገንባት፣

    b) የተማሪዎች እና የሰራተኞች አእምሮዊ እና ስሜታዊ ጤንነት፣

    c) መልካም ያልሆኑ ጭንቀት የሚፈጥሩ የቆዩ አሰቃቂ ሁኔታዎች የተገኙ ልምዶች፣

d) እንደቀድሞው ሁኔታ መልሶ የመገንባት ልምዶች፣

e) አካላዊ ጤንነት እና ደህንነት፣ እና

f) የአዎንታዊ አመለካከት ስነምግባር እድገት እና የሌላውን ችግር ወይም ስሜት መጋራት፣ እንደራስ መመልከት።

5. ተገቢነት ያለው መልካም ባህሪ በመማር የሚጎለብት የእድገት ሂደት ነው፣ እና ውጤታማ የባህሪ ጣልቃገብነት ስልቶች የተማሪን የተለያየ ባህሪ እና የእድገት ፍላጎቶችን ድጋፍ በመስጠት እና በጣልቃገብነቶች እንዲሚሉ ያደርጋሉ። ለሁሉም ተማሪዎች ግላዊ እድገትን እና የመማር እድሎችን የሚደግፍ፣ ተገቢ ላልሆነ የተማሪ ባህሪ ወቅታዊ እና ከእድሜ ጋር የሚመጥን ግብረመልስ መስጠት የመምህራን እና የሥራ ባልደረቦች ሚና ነው።

6. የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ ተማሪዎች ከፌዴራል ህጎች እና ፍትሃዊ ሂደቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ ለሁሉም ተማሪዎች ተገቢውን የአሰራር ሂደት ያመቻቻል/ታመቻቻለች።

7. አዎንታዊ የመልካም ባህርይ/ስነምግባር ጣልቃ ገብነትን መጠቀም አስቸጋሪ ባህርዮችን ከመከላከል ወይም ከመቀነሱም ባሻገር አካደሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ስነልቦናዊ-ስሜታዊ እድገትን ያዳብራል። MCPS ተገቢ፣ ኃላፊነት የሚሰማው እና ውጤታማ ስልቶችን እና መመሪያዎችን በመጠቀም የተማሪን ስነምግባር መምራት እና ሥርዓታማ እና የትምህርት ውጤታማነትን ማመቻቸት አለበት።
በመረጃ ላይ የተመሰረተ እና ከአሰቃቂ ገጠመኝ ሁኔታ መታደግ።

8. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የባህሪ ጣልቃገብነት ስትራቴጂዎችን - የሚጠቀም የማገገሚያ/የተሐድሶ እቅድ፣ እና በመልካም ግንኙነት ላይ ያተኮረ አሠራር ይጠቀማል።

a) ይኼውም የመከላከል እና አስቀድሞ በመንቃት ላይ ያተኮረ ነው።

b) ጠንካራ ግንኙነቶችን መገንባት እና ለት/ቤት ማህበረሰብ ደህንነት መልካም አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የሚጠበቁ ባህርያትን ፍላጎቶች በመግለጽና በማዘጋጀት ላይ አፅንዖት ይሰጣል፣

c) ለት/ቤት ማህበረሰብ ደህንነት አስተዋፅኦ የሚያደርጉትን ግልጽ የመልካም ባህርይ አስፈላጊነትን ለሚጥስ ስነምግባር ምላሽ ለመስጠት በባህርይ ችግር ምክንያት ለደረሰ ማንኛውም ጉዳት ተጠያቂነትን ማስፈን ላይ ያተኩራል፣ እና

d) በአስቸጋሪ ባህሪ ምክንያት የተበላሹትን ግንኙነቶች ተጎጂው(ዋ)ን ግለሰብ በፈቃደኝነት በማሳተፍ ግንኙነትን ለማደስ መንገዶችን ያመቻቻል።

9. ቀጣይነት ያላቸው ውጤታማ፣ ንቁ የማስተማር ስልቶች እና የዲሲፕሊን እርምጃዎች ጤናማ የመማር ማስተማርን እንቅስቃሴ ይደግፋሉ፣ አወንታዊ ባህሪያትን ያዳብራሉ እና የባህሪ ተሐድሶ ጣልቃገብነት ፍልስፍናን እንደሚከተለው ያንፀባርቃሉ።

a) የሚጠበቀውን የስነምግባር ባህሪ እና ማህበራዊ እና ስሜታዊ ብቃቶችን ለማስተማር እና ለመቅረጽ ውጤታማ ስልቶችን በመጠቀም በትምህርት ክፍል የስነምግባር አመራር ክህሎቶችን ለማጠናከር ለት/ቤት ሰራተኞች ስልጠና መስጠት።

b) ማህበራዊ/ስሜታዊ ትምህርትን፣ ባህላዊ ግንዛቤን፣ ችግር መፍታትን እና የግጭት አፈታትን

በተመለከተ መመሪያ መስጠት።

c) እንደ አስፈላጊነቱ ከህብረተሰቡ ጋር በመቀናጀት የመከላከል እና የጣልቃ ገብነት ስልቶችን እና ፕሮግራሞችን ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ።

10. በት/ቤት የሚገኙ ተንከባካቢ-ጎልማሶች ተማሪዎች እርስበርሳቸው ጠንካራ ግንኙነቶችን በመገንባት ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፣ይህም ከትምህርት ቤት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ይበልጥ የሚያመቻች እና በረባሽነት ባህሪ የመሳተፍ እድሎችን ይቀንሳል። በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ከአንድ አዋቂ ጋር ትርጉም ያለው ግንኙነት ያላቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚረብሹ ባህሪያትን የመፍጠር እድላቸው አነስተኛ ስለሆነ ከተማሪዎች ጋር ትርጉም ያለው ግንኙነት ለመፍጠር የት/ቤት ሥራ ባልደረቦች ማበረታታና ዘዴዎችን መፍጠር አለባቸው።

11. የሥራ ባልደረቦች የተማሪን ፍላጎት ለማሟላት መመሪያ፣ ድጋፍ እና መዋቅር ለመፍጠር ከቤተሰቦች እና ከማህበረሰቡ ጋር ይተባበራሉ። የወላጅ/አሳዳጊ አገልግሎት ወይም ኮንፈረንስ በማድረግ ሰራተኞቹ ተገቢ ያልሆነ ወይም የሚረብሽ የተማሪ ባህሪ መረጃ ለመስጠት እና ወላጆች/አሳዳጊዎችን በመለየት እና በመፍትሄዎች ላይ ለመወያየት በማሳተፍ ከሚጠቀሙባቸው ስልቶች ውስጥ ይጠቀሳሉ። የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ለከባድ ባህሪ ግብረመልስ ለመስጠት ለወላጅ/ለአሳዳጊ የማሳወቂያ መስፈርቶችን ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

12. ፍትሀዊ፣ የፀና፣ እና ዘላቂ የስነምግባር ትግበራ ስለሚጠበቅ ተማሪዎችም ምግባረ ብልሹነት/የመጥፎ ተግባር ድርጊቶች ስለሚያስከትሉት ቅጣቶች እንዲያውቁ መደረግ አለበት። ነገር ግን፣ የት/ቤት የስነምግባር ባህሪ ጣልቃገብነት ስልቶች ተማሪዎችን በተቻለ መጠን በመደበኛ የትምህርት መርሃ ግብራቸው ውስጥ ለማቆየት በሚያስችል መከናወን አለባቸው። እገዳዎችና ስንብቶች እንደ መጨረሻ አማራጭ ብቻ መወሰድ አለባቸው።

13. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሰራተኞችን አቅም በመገንባት የስነምግባር ባህሪ ጣልቃገብነት ስልቶች ቀጣይነት ባለው መልኩ ለሁሉም ተማሪዎች በፍትሃዊነት፣ በሚዛናዊነት እና በስኬት መከናወናቸውን ይገመግማል።

a) ለሁሉም ተማሪዎች ከቦርድ ፖሊሲ ACA፣አንፃር አድሎአዊነት፣ ፍትሃዊነት፣ እና የብቁነት ባህል ጋር በማጣመር ፍትሃዊነትን እና ሚዛናዊነትን ለማረጋገጥ ተግባራዊ እርምጃዎችን ግልጽ አድልኦዎችን እና መዋቅራዊ ጉድለቶችን ለመለየት እና ለማስተካከል ብዙ ጊዜ ተለይተው የሚታወቁ ተቋማዊ መሰናክሎች የተማሪዎች እና የሰራተኞች ቡድን በተማሪ ዲሲፕሊን ድርጊቶች ውስጥ ያለምክንያት ወይም ተመጣጣኝ ባልሆነ መልኩ ተለይተው ይታወቃሉ። የት/ቤት ሰራተኞች ግጭቶችን ለመከላከል እና አስፈላጊ ሲሆን ግብረመልስ ለመስጠት፣ የተማሪዎችን ልዩ ልዩ የስነምግባር ፍላጎቶች ለማሟላት እና የባህሪ ጣልቃገብ ፖሊሲዎችን እና ልምዶችን በፍትሃዊነት ለመተግበር የሚያስፈልጉትን ድጋፍ፣ እውቀት እና ክህሎት የታጠቁ ይሆናሉ።

b) ሠራተኞች እንደአስፈላጊነቱ የተማሪን የእድገት ብስለት በተመለከተ ያለውን መረጃ ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ግላዊ አቀራረቦችን በመጠቀም የስነምግባር ባህሪ ጣልቃገብነት ስልቶችን እንዲተገበሩ መታጠቅ እና መደገፍ አለባቸው። የአእምሮ ጤና ተግዳሮቶች፣ እና ሌሎች ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ የህክምና ወይም የአካል ጤና ስጋቶች፣ በባህሪ ውስጥ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ባህላዊ እና የቋንቋ ምክንያቶች፣ እና ውጫዊ ውጥረት ወይም ቀደም ሲል ያጋጠመ የአሰቃቂ ሁኔታ የሚያሳድረው ተፅእኖ፣ ሁከት፣ ቸልተኝነት፣ አደጋ፣ ሽብርተኝነት እና ጦርነት የተማሪን አካላዊ እና ስሜታዊ ጤንነት እና ትምህርትን በብቃት የመሥራት ችሎታ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል።

14. የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በቦርድ ፖሊሲ COA ላይ እንደተደነገገው፣ የተማሪ ደህንነት እና የትምህርት ቤት ደህንነት፣ የተማሪዎች እና የሰራተኞችን ጤንነት፣ ደህንነት፣እና መብቶችን የሚጠብቅ ጤናማ የስራ እና የትምህርት አካባቢን የሚጠብቅ አጠቃላይ የደህንነት እቅድ እንዲተገበር ያደርጋል።

15. የጽሁፍ ስምምነቶች የህግ አስከባሪ ሰራተኞችን አወንታዊ የትምህርት ቤት ድባብ ለመደገፍ ጠቃሚ የአጋርነት ሚና ስላላቸው ሀላፊነት የተሞላበት ግልጽ የሆኑ የአሠራር መርሆችን ያስቀምጣሉ፣ አላስፈላጊ እስራት እና የፍትህ ስርዓቱን በአግባቡ አለመተግበር በተማሪዎች እና በቤተሰቦቻቸው ላይ ያልተፈለገ አሉታዊ መዘዝ ሊያስከትል ይችላል እንዲሁም በቀለም ተማሪዎች እና በአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ላይ ያልተመጣጠነ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል። የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያ፣ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የስቴት አቃቤ ህግ ቢሮ እና ከሌሎች የህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች ጋር እነዚህን ስምምነቶች ለመገምገም፣ ለመተግበር እና ለማዘመን ይሰራል።

16. ***ተፈላጊ ውጤቶች***

   1. ትምህርት ቤቶች አዎንታዊ፣ አክብሮት የተሞላበት፣ በሥነ ሥርዓት የታነጸ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢዎችን እንዲያዳብሩ ይጠበቃል፣ይኼውም አረአያነት ያለው እና በጋራ የመግባባት እና የመከባበር አካባቢ ማለት ነው።

   2. ወላጆች/አሳዳጊዎች/ቤተሰቦች እና ተማሪዎች ስለትምህርት ቤት ስነምግባር የማስተዳደርና የመምራት ፖሊሲዎች በደንብ ይገለጽላቸዋል፤ እንዲሁም ትምህርት ቤቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ሥርዓት የሚከበርባቸው ተቋማት መሆናቸውን ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት እንዲሳተፉ ይበረታታሉ።

   3. ተማሪዎች የስነምግባር ባህሪ ጣልቃገብነት ስትራቴጂዎችን በተመለከተ ኃላፊነታቸውን እና መብቶቻቸውን እንዲገነዘቡ ይደረጋል።

   4. የትምህርት ቤት የስነምግባር ባህሪ ጣልቃገብነት ስልቶች በፍትሃዊነት፣ በእኩልነት፣ እና በቋሚነት ይከናወናሉ/ይመራሉ።ትምህርት ቤቶች የፖሊሲዎችን የተዛባ እና ያልተመጣጠነ ተፅዕኖ ማስወገድ አለባቸው።

   5. የት/ቤት የስነምግባር ባህሪ ጣልቃገብነት ስትራቴጂዎች ጠንካራ ግንኙነቶች ላይ አፅንዖት በመስጠት ተማሪዎች በክፍል መስተጋብሮች ላይ እንዲሳተፉ፣ ለት/ቤቱ ማህበረሰብ ደህንነት አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ፣እና ከ MCPS ለኮሌጅ እና ለስራ ዝግጁ ሆነው እንዲመረቁ ከባህሪያቸው የሚጠበቁ ቁምነገሮችን ግልጽ ያደርጋሉ።

D. ***የአተገባበር መመሪያዎች***

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለሁሉም ተማሪዎች እና ለወላጆቻቸው/አሳዳጊዎች/ቤተሰቦቻቸው የሚቀርብ ዲስትሪክት አቀፍ የተማሪዎች የስነምግባር ደንብ ያዘጋጃል።

2. እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ቤተሰቦችን፣ ተማሪዎችን እና ሰራተኞችን በማሳተፍ የራሱን የስነምግባር ደንብ ሲያዳብር በየጊዜው ግብረ መልሶችን በማካተት ከአፈፃፀሙ አንፃር ይገመግመዋል። በትምህርት ቤት ደረጃ ኮዶችን በማዘጋጀት የማህበረሰብ ተሳትፎ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ቤተሰቦች የተማሪዎችን ባህሪ እና የስነምግባር ጣልቃገብነት ስትራቴጂን በተመለከተ ሚናቸውን፣ ኃላፊነታቸውን እና መብቶቻቸውን እንዲገነዘቡ ሊረዳቸው ይችላል። የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ ከዚህ መመሪያ አኳያ MCPS ደንቦች፣ ዲስትሪክት አቀፍ የተማሪዎች የስነምግባር ደንብ፣ እንዲሁም የሚመለከተውን የፌዴራል እና የስቴት ህጎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የእያንዳንዱን ትምህርት ቤት የስነ ምግባር ደንብ ይገመግማል።

3. የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማህበረሰብ ደህንነት እና አስጊ ጉዳዮችን ይከታተላል እና እንደአስፈላጊነቱ ለትምህርት ቦርድ ሪፖርት ያደርጋል።

4. የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የስነምግባር ባህሪ ጣልቃገብነት መረጃዎችን በትምህርት ቤቶች የሚከናወኑትን ጣልቃገብነቶች እና ፕሮግራሞችን ለመገምገም እና ማናቸውንም የተዛባ እና ያልተመጣጠነ የስነምግባር ባህሪ ጣልቃገብነት ስትራቴጂዎችን ተፅእኖ ለመፍታት የሚወሰዱ እርምጃዎችን ይቆጣጠራል።

E. ***ግምገማ እና ሪፖርት***

ይህ ፖሊሲ በቦርዱ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሰረት ይገመገማል።

***ተዛማጅ ምንጮች:*** Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-306; Code of Maryland Regulations 13A.08.03-.04; Student Code of Conduct in MCPS

**የፖሊሲው ታሪክ፡** በውሳኔ ቁጥር 20-97 ተግባራዊ እንዲደረግ ተወሰነ ጃኑዋሪ 14/1997 በውሳኔ ቁጥር ...ተሻሽሏል 9-15፣ ጃኑዋሪ 13, 2015 በውሳኔ ቁጥር ...ተሻሽሏል 188-22፣ ኤፕሪል 7, 2022።